# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ብቁነት

1. **ለዚህ የስጦታ ፕሮግራም ለማመልከት ብቁ የሆነው ማነው?**
   በቀጥታ በሆነ መልኩ በ COVID-19 ምክንያት ከገቢው ላይ የ 25% ወይም ከዚያ በላይ ኪሳራ የደረሰበት በአሌክሳንድሪያ ከተማ ውስጥ እንዲሰራ የተመዘገበ በአካባቢው ያለ ማንኛውም አነስተኛ ትርፋማ የየንግድ ድርጅት ተቋም ነው። ብቁ ሆኖ ለመገኘት አመልካቾች የሚከተሉትን **<u>ሁሉንም</u>** መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡
   - በአሌክሳንድሪያ ከተማ የኮርፖሬት ወሰን ውስጥ የሚገኙ
   - ከአሌክሳንድሪያ ከተማ የተሰጠ የጸና ንግድ ፈቃድ ያለው
   - ከማርች 1/2019 ጀምሮ ስራ ላይ የሚገኝ
   - ለትርፍ የተቋቋመ አካል
   - የንግድ ድርጅቱ ከአሌክሳንድሪያ ከተማ ጋር "በመልካም አቋም" ላይ ያለ ይህም ማለት ሁሉንም ወቅታዊ የታክስ ክፍያዎች የከፈለ
   - በአሌክሳንድሪያ ውስጥ የንግድ ድርጅቱ በስራ ላይ ሆኖ ከዲሴምበር 31/2020 በኋላም ይቆያል
   - ከዲሴምበር 31/2019 ጀምሮ የንግድ ድርጅቱ ቢያንስ 2 ቢበዛ ደግሞ 100 W-2 ሰራተኞችን ይቀጥራል
   - በኮቪድ 19 የተነሳ የንግድ ድርጅቱ የ 25% ወይም ከዛ በላይ አጠቃላይ የገቢ ማሽቆልቆሉን ማሳየት አለበት።

2. **ለዚህ ፕሮግራም ለማመልከት ብቁ ያልሆነው ማነው?**
   ሁሉንም የብቁነት መስፈርት ያላሟላ ማንኛውም የንግድ ድርጅት ወይም ተቋም። ይህ ፕሮግራም ለትርፍ ለማይሰሩ ድርጅቶች ወይም የግል ባለቤቶች ክፍት አይደለም። የሚከተሉት የንግድ ድርጅቶች ፕሮግራሙ ላይ መሳተፍ እንዳይችሉ ተለይተዋል፡
   - የሽቀጣ ሸቀጥ መደብሮችና ፋርማሲዎች
   - የነዳጅ ማደያዎች
   - ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት
   - በኮርፖሬሽን የተያዙ ቦታዎች፣ ቅርንጫፎች ወይም ንኡስ ክፍሎች እንዲሁም በአካባቢው ነዋሪ የተያዙና ስራ ላይ ያሉ ካልሆኑ በስተቀር የፍራንቻይዝ ቢዝነሶች

3. **ለትርፍ የማይሰሩ ድርጅቶች በፕሮግራሙ ለምን አልተካተቱም?**
   አሁን ያለው የገንዘብ ድጋፍ ቅድሚያ እየሰጠ ያለው በ COVID-19 ምክንያት እየተጎዱ የሚገኙ አነስተኛ ቢዝነሶችን መደገፍ ነው። ባለው የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ ሁኔታ መሰረት የፕሮግራም መስፈርቶቹ የተመሰረቱት ለህብረተሰቡ ከፍተኛ የኢኮኖሚና የስራ እድል ለሚያቀርቡ አነስተኛ ቢዝነሶች ቅድሚያ ለመስጠት ነው። ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ከተገኘ በአሌክሳንድሪያ በሙሉ ተጨማሪ የኢኮኖሚክ ድጋፍ ለማድረግ የብቁነት መስፈርቱ ሊለወጥ ይችላል።

4. **የግል ባለቤቶች በፕሮግራሙ ለምን አልተካተቱም?**

አሁን ያለው የገንዘብ ድጋፍ አነስተኛ ቢዝነሶችን ለረጅም ጊዜ ለመደገፍ ቅድሚያ ሰጥቶ ቀጣይነት ያለው የስራ እድል የሚፈጥር ነው። ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ከተገኘ በአሌክሳንድሪያ በሙሉ ተጨማሪ የኢኮኖሚክ ድጋፍ ለማድረግ የብቁነቱ መስፈርቱ ሊለወጥ ይችላል።

**5. የንግድ ድርጅቴ በአሌክሳንድሪያ ከተማ ፈቃድ አልተሰጠውም፣ ለስጦታው ለማመልከት ብቁ ሆኜ እገኛለሁ?**
አይ፣ ለስጦታው ብቁ ሆነው የሚገኙት አሁን በአሌክሳንድሪያ ከተማ የየንግድ ድርጅት ፈቃድ ያላቸውን የቀሩትን መስፈርቶች በሙሉ የሚያሟሉ ቢዝነሶች ብቻ ናቸው።

**6. አንድ የንግድ ድርጅት ብቁ ለመሆን ከማርች 1/2019 ጀምሮ በስራ ላይ መሆን ያለበት ለምንድን ነው?**
የ COVID-19 ተጽእኖን በተመሳሳይ መንገድ መለካቱን ለማረጋገጥና በየንግድ ድርጅት እንቅስቃሴዎች ያሉ ወቅታዊ መለዋወጦችን ከግምት ውስጥ ለማስገባት በየአመቱ (year-over-year) ያሉ አጠቃላይ ገቢን ፕሮግራሙ እንዲያነጻጽር ይጠይቃል። የጤና አደጋ ጊዜው የጀመረው በማርች 2020 ሲሆን የአመቱን (year-over-year) ንጽጽር ለማቅረብ አንድ የንግድ ድርጅት ማርች 2019 ላይ ስራ ላይ ሊኖር ይገባዋል።

**7. አንድ የንግድ ድርጅት "ጥሩ አቋም" ላይ መኖር አለበት ሲባል ምን ለማለት ነው?**
አንድ የንግድ ድርጅት "ጥሩ አቋም" ላይ መኖር አለበት ሲባል ከአሌክሳንድሪያ ከተማ ጋር በሁሉም የታክስ ክፍያዎች ላይ ወቅታዊ ከነበሩ ነው። ነገር ግን ይህ የማያጠቃልለው ማንኛውም የተላለፈ የአሁን አመት የየንግድ ድርጅት ታክሶች ወይም ከፌብሩዋሪ 1 እስከ ጁን 30/2020 ያለው የከተማው ጊዜያዊ እገዳ ስር ያለ የግብር ምዝገባ ነው።

**8. 25% ወይም ከዛ በላይ የአጠቃላይ ገቢ ኪሳራ የሚሰላው እንዴት ነው?**
የንግድ ድርጅቶች የማርች፣ ኤፕሪልና ሜይ 2019 እና 2020 ወርሃዊ አጠቃላይ ገቢ (ማለትም ከማንኛውም ወጪዎች በፊት የገኘ ገቢ/ሽያጭ) ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

በመጋቢት፣ ሚያዝያና ግንቦት 2020 ያሉት አጠቃላይ ገቢዎች በ2019 ካሉት ተመሳሳይ ወራት ገቢዎች ጋር ይነፃፀራል። ብቁ ለመሆንና የገቢ ኪሳራ ብቁነት መስፈርትን ለማሟላት፣ 25% ወይም ከዛ በላይ ከሶስቱ ወራት በአንዱ ላይ (ከ 2019 ከነበረው ተመሳሳይ ወራት ጋር ሲነፃፀር) አጠቃላይ የገቢ ማሽቆልቆል የደረሰበት መሆን ይኖርበታል።

**9. እንደ ተጣራ ትርፍ ካሉት ይልቅ የገቢ ማሽቆልቆልን ለመለካት አጠቃላይ ገቢዎች ለምን ጥቅም ላይ ይውላሉ?**
አጠቃላይ ገቢ ወይም ሽያጮች ምክንያት በመሆን እና የድርጅቶችን የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ምርጥ መለኪያዎች ናቸው። የተጣራ ገቢን የመሳሰለ መለኪያ በእቃዎች ዋጋ ላይ ወይም ከንግድ ድርጅቱ ጋር የተገናኙ ወጪዎች ላይ ተመርኩዞ ሊቀያየር ይችላል። በየአመቱ (year-over-year) አጠቃላይ ገቢን ማነፃፀር COVID-19 በየንግድ ድርጅት እንቅስቃሴ ላይ ያደረሰውን ትክክለኛ ተጽእኖ ለመለካት ያስችላል።

**10. W-2 ሰራተኞች ብቻ ለምን በሰራተኛ ቁጥር ውስጥ ይያዛሉ? 1099 የስራ ተቋራጮችስ?**
ባለው የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ ሁኔታ መሰረት መስፈርቶቹ የተመሰረቱት ለህብረተሰቡ ከፍተኛ የኢኮኖሚና የስራ እድል ለሚያቀርቡ አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ቅድሚያ ለመስጠት ነው። አሁን ያለው የገንዘብ ድጋፍ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሰራው ሙሉ በሙሉ ቅጥር ወይም ትርፍ ጊዜ ቋሚ የስራ እድል ላቀረቡ አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ነው። ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ከተገኘ በአሌክሳንድሪያ በሙሉ ተጨማሪ የኢኮኖሚክ ማገገም እንዲኖር ለማድረግ የብቁነት መስፈርቱ ሊለወጥ ይችላል።

**11. የሙሉ ጊዜና የትርፍ ጊዜ W-2 ሰራተኞች በሰራተኛ ቁጥር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ?**
አዎ፣ እያንዳንዱ የ W-2 ሰራተኛ ምንም ያህል ሰዓት በሳምንት ውስጥ ቢሰራም እንደ (1) ሰራተኛ ይቆጠራል።

**12. የሰራተኞቼን ቁጥር ለመቁጠር የተለየ ቀን መጠቀም ይኖርብኛል?**
አዎ፣ የሰራተኛ ቆጠራው ከ ዲሴምበር 31/2019 ጀምሮ መሆን ይኖርበታል። አመልካቾች የ IRS ቅጽ 941 ኮፒ ለ2019 የሂሳብ ዓመት 4ኛ ሩብ ዓመት እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ ይህም የየንግድ ድርጅቱን የ W-2 ሰራተኞችን ቁጥር ለማረጋገጥ ይጠቅማል።

13. **የንግድ ድርጅት ባለቤቱ (ባለቤቶቹ) የሰራተኞች ቁጥር ውስጥ ይካተታል?**
አዎ። ምንም እንኳን በደሞዝ ላይ (ማለትም የ W-2 ሰራተኛ ያልሆነ) ባይካተቱም እስከ አንድ የንግድ ድርጅት ባለቤት ለስጦታው ብቁ እንዲሆን ለማገዝ  በአጠቃላይ የሰራተኛ ቁጥር ውስጥ ይጠቃለላል። ነገር ግን የየንግድ ድርጅት ባለቤቱን እንደ ሰራተኛ መቁጠር ሰራተኞች እንዲበዙ በማድረግ የንግድ ድርጅቱን ብቁ እንዳይሆን ካደረገው፣ የየንግድ ድርጅት ባለቤቱ ላይቆጠር ይችላል።

14. **የንግድ ድርጅቴ በኪሳራ ሂደት ውስጥ ካለ ብቁ ልሆን አልችልም?**
አዎ።

15. **ለስጦታዎች፣ለብድር ወይም ሌላ ድጋፍ ከፌዴራል የአደጋ ፕሮግራሞች(federal disaster programs) ወይም ሌላ ምንጮች ካመለከትኩ የንግድ ድርጅቴ አሁንም ብቁ ሊሆን ይችላል?**
አዎ፣ ብቁ የሆኑ ቢዝነሶች ሆነው በፌዴራል የኢኮኖሚ ጉዳት አደጋ ብድር (EIDL) ወይም የደመወዝ ክፍያ መከላከል ፕሮግራም (PPP) ወይም ሌላ መንግስታዊ ያልሆኑ ምንጮች ስጦታ ላይ ያመለከቱ በዚህ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ይችላሉ።  በ EIDL እና PPP ፕሮግራም ውስጥ የሚገኙ የገንዘብ ድጋፎች በድርጅቱ የሂሳብ ወረቀት ላይ በአሌክሳንድሪያ B2B የስጦታ ፕሮግራም ምክንያት እንደ ገቢ አይቆጠሩም።

## የማመልከቻ ሂደት

1. **ለማመልከት ኮምፒውተር ያስፈልገኛል?**
አዎ፣ ኢንተርኔት ያለው ኮምፒውተር ያስፈልግዎታል ምክንያቱም ይህ ማመልከቻ የሚሞላው ኦንላይን ላይ ነው። የግብር ተመላሾች (tax returns) እና የፋይናንስ ሰነዶች በዲጂታል ኮፒ ከሌለዎት፣ ስካነር ማግኘት ይኖርብዎታል። ማመልከቻው አንዴ ከተቀመጠ በኋላ ካቆሙበት መቀጠል አይቻልም።

2. **ማመልከቻዬን በፖስታ መላክ፣ ኢሜይል ወይም ፋክስ ማድረግ ወይም የሆነ ቦታ ላይ ማስቀመጥ እችላለሁ?**
አይችሉም፣ ማመልከቻዎች በኦንላይን ማስገቢያ በኩል ብቻ ይደርሳሉ።

3. **መቼ ላመለክት እችላለሁ እንዲሁም የማመልከቻው የመጨረሻ ቀን መቼ ነው?**
ማመልከቻዎች ከጁን X/2020 8:00 AM EDT ጀምሮ alexandriaecon.org ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ እስከ ጁን X/2020 5:00 PM EDT ድረስ ክፍት ሆኖ ይቆያል።

4. **የኦንላይን ማመልከቻውን የት ላገኝ እችላለሁ?**
ማመልከቻው በ https://alexandriaecon.org/alx-b2b/application/ላይ ይገኛል።

5. **ከማልከቻዬ ጋር ማስገባት የሚኖርብኝ ተጨማሪ መረጃ ምንድን ነው?**
ኦንላይን ማመልከቻውን እንደጨረሱ የሚከተሉትን ሰነዶች መጫን ማድረግ ይኖርብዎታል፡
   - ከንግድ ድርጅቱ ጋር የተገናኘ የፌዴራል የአሰሪ መለያ ቁጥር  (FEIN) ወይም የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር (SSN)
   - የአሌክሳንድሪያ የንግድ ስራ ፕሮፌሽናል ይዞታ ፈቃድ መለያ ቁጥር
   - IRS ቅጽ 941 ለ2019 የሂሳብ ዓመት 4ተኛ ሩብ ዓመት
   - የማርች፣ ኤፕሪል እና ሜይ 2019 እንዲሁም የማርች፣ ኤፕሪልና ሜይ 2020 ዝርዝር ወርሃዊ ትርፍና ኪሳራ መግለጫ (እንደአማራጭ በመግለጫ ምትክ  በነዚህ ተመሳሳይ ጊዜያት ያሉ የባንክ መግለጫዎችን ማስገባት ይቻላል)
   - የንግድ ኪራይ ላለበት የንግድ ድርጅት የአሁኑ ሊዝ የሚያቃበት ቀን።

6. **ማመልከቻው በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛል?**

አይ፣ ማመልከቻው በእንግሊዝኛ መቅረብ ይኖርበታል። የስፓኒሽ፣ አማርኛና አረብኛ የማመልከቻ ኮፒዎች ከማመልከቻው ጊዜ ቀደም ብሎ በhttps://alexandriaecon.org/alx-b2b/application/ ላይ ማውረድ ይቻላል።

7. **ማመልከቻዬ መድረሱን የሚያሳይ ማረጋገጫ አገኛለሁ?**
   አዎ፣ ማመልከቻው ገቢ እንደተደረገ ለአመልካቹ የኢሜል ማረጋገጫ ይላክለታል።

8. **የክለሳው ሂደት ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**
   የማመልከቻ ጊዜው ልክ ጁን 8/2020 በ 5:00 PM EDT ላይ ሲዘጋ የክለሳው ሂደት ወዲያውኑ ይጀመራል። ሁሉንም ማመልከቻዎች ለማየትና የግራንት ውሳኔዎችን ለመወሰን በግምት ከ 2-3 ሳምንታት ይፈጃል። የፕሮግራሙ ግብ የገንዘብ ድጋፉን በጁላይ መጀመሪያ ላይ ለንግድ ድርጅቶች ማስተላለፍ ለመጀመር ነው።

   የሚቀርበው ማመልከቻ ዝግጁ ከሆነው ገንዘብ በላይ እንደሚሆን ይጠበቃል። ብዙ መጠን ያለው ማመልከቻ የክለሳውን ሂደት ሊያስተጓጉለው ይችላል። AEDP ማንኛውም የክለሳና የፈቀደውን የጊዜ ሰሌዳ ለውጦች በ ALX B2B የግራንት ፕሮግራም ድረ ገፅ https://alexandriaecon.org/alx-b2b/ላይ ያሳውቃል።

9. **የማመልከቻዬን ሁኔታ እንዴት ማየት እችላለሁ?**
   ሁሉም አመልካቾች ማመልከቻቸው ሲገባና የመጨረሻ የስጦታው ውሳኔ ሲወሰን መልእክት ይደርሳቸዋል። AEDP አጠቃላይ የፕሮግራም ወቅታዊ መረጃዎችን በድረ ገጻችን (www.alexandriaecon.org) ላይ እና በኢሜይል ዜና ማንቂያችን በሚፈለገው ያህል እናቀርባለን።

10. **የንግድ ድርጅት መረጃዎቼን ማግኘት የሚችለው ማነው?**
    የዚህ ፕሮግራም አካል የሆነ ሁሉም መረጃ ሚስጥራዊነቱ እንደሆነ ይያዛል እንዲሁም በክፍል 2.2-3705.6 እና 58.1-3 የቨርጂኒያ ደንብ መሰረት ይጠበቃል፣ ስለሆነም ከዚህ የግራንት ፕሮግራም አስተዳደር ውጪ መረጃው አይጋራም። ከአሌክሳንድሪያ የኢኮኖሚ ልማት አጋርነት (Alexandria Economic Development Partnership) የመጡ ሰራተኞች ይህንን ፕሮግራም ያስተዳድራሉ። የማመልከቻውን ክለሳ እንዲያደርጉ የተመረጡ ሰራተኞች በንግድ ድርጅቱ ላይ የተቀመጠውን መረጃ ያገኛሉ። በተጨማሪም የአሌክሳንድሪያ ከተማ የፋይናንስ መምሪያ ሰራተኞች የንግድ ድርጅቶች የሚያቀርቡትን መረጃዎች ለመከለስ ይሳተፋሉ። በመጨረሻም AEDP የአመልካቹን የፋይናንስና የግብር መረጃ ለመከለስ እንዲያግዝ በማሰብ ሶስተኛ ወገን ተቋም ቀጥሯል።

11. **የግሌ እና የየንግድ ድርጅት መረጃዎቼ ሚስጥራዊነቱ ይጠበቃል?**
    አዎ፣ የዚህ ፕሮግራም አካል የሆነ ሁሉም መረጃ ሚስጥራዊነቱ እንደሆነ ይያዛል እንዲሁም በክፍል 2.2-3705.6 እና 58.1-3 የቨርጂኒያ ደንብ መሰረት ይጠበቃል፣ ስለሆነም ከዚህ የግራንት ፕሮግራም አስተዳደር ውጪ መረጃው አይጋራም።

## የግራንት ገንዘብ

1. **የንግድ ድርጅቴ ምን ያህል የገንዘብ እርዳታ ሊያገኝ ይችላል?**
   አጠቃላይ በተረጋገጠው የሰራተኛ ቁጥር መሰረት ሶስት አይነት የግራንት ደረጃዎች አሉ፡

| የሰራተኛ ቁጥር | የግራንት መጠን |
|---|---|
| 2-24 | $10,000 |
| 25-49 | $15,000 |
| 50-100 | $20,000 |

2. **የገንዘብ እርዳታው ለምን ጥቅም ይውላል?**
   የ ALX B2B ግራንት የንግድ ድርጅቶችን መልሶ ከመክፈትና ከማቋቋም ጋር የተገናኙ ወጪዎች እና/ወይም ኢንቨስትመንቶችን ለማካካስ መዋል አለባቸው። ከግራንቱ የሚገኘው ገንዘብ ለሚከተሉት ዕቃዎች ግዥ የሚውል ነው፡
   - የ COVID-19 ስርጭትን ለማስቆም የሚረዱ የግል ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች (PPE)
   - ጤና እና ደህንነትን ለማሳደግ የሚውሉ ሌሎች መሳሪያዎችና አቅርቦቶች

- የ ኢ-ኮሜርስ እና/ወይም የቨርቹዋል የንግድ ድርጅት እንቅስቃሴዎች (በጃንዋሪ 1/2020 እና ከዚያ በኋላ የተገዛ ቴክኖሎጂ ተመላሽ ገንዘብ ለማግኘት ብቁ ሊሆን ይችላል)
- አካላዊና ማህበራዊ መራራቅን ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ በንግድ ድርጅቱ ነባር አካባቢ ላይ የሚከናወኑ ዲዛይንና ግንባታ/ለውጥ ጋር የተያያዙ የባለሙያ አገልግሎቶችና ለለውጦቹ በተጨባጭ የወጡ ወጪዎች
- ድርጅቱን ዳግም ለመክፈት/ስራ ለማስጀመር የሚያስፈልጉ የኪራይ ወይም የወለድ አገድ ወጪዎች።

3. **የገንዘብ ድጋፉን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የተቀመጡ ገደቦች አሉ?**
የተሰጠው የገንዘብ ድጋፍ ኢንቨስትመንቶችን በማድረግ የንግድ ድርጅት እንደገና እንዲከፈትና እንዲሰፋ የሚያግዝ ነው። የተከለከሉ አጠቃቀሞች መካከል ከሚጠቃለሉት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡ የደመወዝ ወጪዎች፣ የእዳ ክፍያዎች፣ እንዲሁም የአካባቢ፣ የግዛት ወይም የፌዴራል ታክስ ናቸው።

4. **ይህ የአንድ ጊዜ ክፍያ ነው?**
አዎ፣ የገንዘብ ድጋፉ የሚተላለፈው በአንድ ጊዜ ክፍያ ነው።

5. **ገንዘቡን መልሼ መክፈል ይጠበቅብኛል?**
አይ፣ ይህ ስጦታ ብድር አይደለም ስለዚህ የስጦታውን ሁሉንም ውሎችና ሁኔታዎች ከጠበቁ የገንዘብ ድጋፉን መመለስ አይጠበቅብዎትም።